March 2018 ቁጥር 3

# ዳግማዊ ሰንሰለት



በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አማኞች፣ ወዳጆችና የቀድሞ አድቬንቲስት ት/ቤት ተማሪዎች በየሶስት ወሩ የሚወጣ

## አንፈራም

አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፥ ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው። ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ ... **አንፈራም**። መዝሙር 46:1-2

### ለምንድነው የማንፈራው?

| | |
|---|---|
| ክርስቶስ ፋሲካችን ስለሆነ | 1ቆሮንቶስ 5:7 |
| ክርስቶስ ሰላማችን ስለሆነ | ኤፌሶን 2:14 |
| የሱስ ጠበቃችን ስለሆነ | 1 ዮሐንስ 2፡1 |
| የሱስ የህይወት እንጀራችን ስለሆነ | ዮሐንስ 6:35 |
| ክርስቶስ የማእዘኑ ድንጋያችን ስለሆነ | ኤፌሶን 2:20 (መዝሙር 118:22) |
| የሱስ መልካሙ እረኛችን ስለሆነ | ዮሐንስ 10:11 (መዝሙር 23) |
| የሱስ ታላቁ ሊቀ ካህናችን ስለሆነ | ዕብራውያን 4:14 |
| የሱስ ብርሃናችን ስለሆነ | ዮሐንስ 8:12 |
| የሱስ ድል ነሻችን ስለሆነ | ራዕይ ዮሐንስ 5:5 |
| የሱስ አስታራቂያችን (አማላጃችን) ስለሆነ | 1ጢሞቴዎስ 2:5 |
| ክርስቶስ ተስፋችን ስለሆነ | 1ጢሞቴዎስ 1:1 |
| ክርስቶስ መንፈሳዊ ዕለታችን ስለሆነ | 1ቆሮንቶስ 10:4 |
| የሱስ በራችን ስለሆነ | ዮሐንስ 10:9 |

### ስለዚህ

**ጠላቴ ሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ። ሚኪያስ 7:8**

ዳንኤል ኃይለማርያም (ስዊድን)
ዋና አዘጋጅ

## የዚህ ዕትም ይዘት ገጽ

| | |
|---|---|
| አንፈራም (ከአዘጋጁ) | 1 |
| የትዳርና ማህበራዊ ኑሮ ሚስጥር | 2 |
| እንዲህ እንዲህ ሆነ (ክፍል አንድ) | 2 |
| እንደምን አደጋችሁ (ቋሚ አምድ) | 4 |
| ድር ቢያብር አንበሳ ያስር | 5 |
| የክርስቶስ ደብዳቤዎች | 6 |
| ማስታወቂያዎች | 8 |
| ዳግማዊ ሰንሰለት | 8 |

**የሚቀጥለው ዕትም ጁላይ 2018 ላይ ይበተናል።**

**የፅሁፍ አስተዋፅኦ በደስታ እንቀበላለን**

### ዳግማዊ ሰንሰለት

በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አማኞች፣ ወዳጆችና የቀድሞ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየሶስት ወሩ የሚበተን የኤሌክትሮኒክ መጽሔት

### ዳግማዊ ሰንሰለት መነሻ (መሰረት)

1) የአንድ አገር ዜጎችና የእግዚአብሔር ቤተሰዎች መሆናችን (ኤፌ. 2፥19)
2) የየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ግድ ሲለሚለን (2ቆሮ. 5፥14)

### ዳግማዊ ሰንሰለት ዓላማ

1) ገንቢ የሆኑ መልእክቶችን ማስተላለፍ
2) መንፈሳዊ አንድነትንና ህብረትን ማጠናከር
3) ራሳችንን እና ሌሎችን ለእግዚአብሔር መንግስት ማዘጋጀት
4) እግዚአብሔር የሚከብርበትንና የሚታይበትን አገልግሎት ማበርከት



## የመልካም ትዳርና ማህበራዊ ኑሮ ሚስጥር

**ያዕቆብ 1:19**

**ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ሆይ፥ ሰው ሁሉ**

### ለመስማት የፈጠነ ይሁን

(ሁለት ጆሮ የተሰጠን ያለነገር አይደለም)
ለማስተዋል የፈጠነ፡ ለመረዳት የፈጠነ፡ ለመጠየቅ የፈጠነ፡ ነው እንዴ ለማለት የፈጠነ፡ እሺ ለማለት የፈጠነ፡ መልካሙን ለማየት የፈጠነ፡ ለማስተዋል የፈጠነ፡ ሁኔታውን ከብዙ አቅጣቻ ለመረዳት የፈጠነ

### ለመናገርም የዘገየ ይሁን

(አንድ አፍ የተሰጠን ያለነገር አይደለም)
ለመመለስ የዘገየ፡ ለመተቸት የዘገየ፡ ለመተርጎም የዘገየ፡ ለማጥቃት የዘገየ

### ለቍጣም የዘገየ ይሁን

ለምላሽ የዘገየ፡ ለመጉዳት የዘገየ፡ ለማጥቃት የዘገየ፡ ለመበቀል የዘገየ፡ ቱግ ለማለት የዘገየ

## ጌታ የሱስ ሆይ እርዳን



## እንዲህ እንዲህ ሆነ (ክፍል አንድ)

መረቡን ዘርግቶ ዓሳ በመሰብሰብ ጀልባ እየቀዘፈ
ኑሮን የሚገፋ፣ በገሊላ ባህር እየተንሳፈፈ
ስምኦን የተባለ  ኋላም ኬፋ፣ ጴጥሮስ
ይህ ነበር ታሪኩ ሲያገኘው ኢየሱስ

አንድ ቀን ኢየሱስ  ወደጴጥሮስ መጥቶ
በእሱ ውስጥ ያለውን ጸጋ ተመልክቶ
አሳን ኣሳንሶ፣ መረብህን ጣል አለው መረቡን አስጣለው
"ና እና ተከተለኝ ሰውን ታጠምዳለህ" ብሎ አስከተለው

ከኢየሱስ አጠገብ ሁሌ የማይጠፋው
ፈጣን ተናጋሪ እሳት የላሰ ሰዉ
ከደቀመዎቹ ቀዳሚዉ ሚኒስተር ማን ነው ከተባለ
ማን ሊሆን ይችላል ጴጥሮስ እዛ እያለ!

የሆነ ሰዓት ላይ እንዲህ እንዲህ ሆነ
መምህሩ ጠየቀ፣ ተሜም ተፈተነ

መምህሩ፡ "ያ ሁሉ መንጋ ህዝብ እኔን ማን ነው ይላል?"

ተሜዎቹም አሉ፡ "ኤልያስም ዮሐንስ አንዳንዱም ኤርምያስ
ብቻ ይለያያል ከህዝቡ ያለዉ መልስ"

"እሺ እናንተስ እኔን ማን ነኝ ትላላችሁ?
ማን እንደምትሉኝ መልሱ ልስማችሁ"
ጴጥሮስ ፈጠን ብሎ እጁን አወጣና
"ስማማ ልንገርህ አንተ ማን እንደሆንክ
ከህያዉ እግዚአብሐር ወደእኛ የተላክ
አንተ ክርስቶስ ነህ የሚመጣዉ መሲህ
እኔ አውቄሃለሁ ገና ስከተልህ"

መምህሩም አላቸው፡"አንተ የዮና ልጅ ስምኦን ጴጥሮስ ሆይ
ይህን ታላቅ ሚስጥር የሰጠህ ከሰማይ
አባቴ ነው እንጅ ሌላ ሰው አይደለም
አይገኝምና ከስጋና ከደም"
ጴጥሮስ ተኮፈሰ፣ በጣምም ሞቅ አለው
ሚስጥር በማወቁ ከፍ ያለ መሰለው

የሆነ ሰዓት ላይ እንዲህ እንዲህ ሆነ
መምህሩ አፉን ከፍቶ፣ መናገር ጀመረ
"የሰው ልጅ ይሄዳል ወደ ኢየሩሳሌም
መከራን ሊቀበል ሊገደል ሊናቅም
ከሞት ግን ይነሳል በሦስተኛው ቀን
ይህ ሊሆን ግድ ነው፣ ዓለም እንዲድን"

"እምም..." አለ ጴጥሮስ
የሱስን እያየ በግሳጼ መንፈስ
"ና" አለው ኢየሱስን፣ ኮስተር አርጎ ፊቱን
"ጌታ ሆይ! ይሄ አይደርስብህም፣ ከቶ አይሆንብህም
እንዲህ ያለ ነገር፣ ፈጽሞ አትናገር"
እያለ ይገስጸው ጀመር፣ ያን ታላቁን መምህር!

# እንዲህ...

መምህሩም መለሰ፣ ለጴጥሮስ እንዲህ ሲል
”አንተ ሰይጣን! ወደኋላዬ ሂድ እንቅፋት አትሁነኝ
የእግዚአብሔርን ትተህ የሰው አትንገረኝ
ለምን አትማርም ከደቃቃዋ ዘር
በስብሳን አይደለም ቁጥር የምትጨምር?
እኔም እልሃለሁ ሰው ነፍሱን ቢያጠፋ
ከእኔ ጋር ለመሆን ይኖረዋል ተስፋ”

ሌላ ጊዜ ደግሞ  እንዲህ እንዲህ ሆነ
ደቀመዛሙርቱ ልባቸው ተከነ
እነዚያ ነጎድጓድ የዘብዲዎስ ልጆች
በእናታቸው በኩል ስልጣን ፈላጊዎች
አንዳቸውም በቀኝ አንዳቸው በግራ
መሆንን ፈልገዉ በዘየዱት ሴራ
አስሩ ሰሙና እሪታ ቀለጠ
ድብቁ **እኔነት** እራሱን ገለጠ
ሁሉም ተባባሉ ”መምህሩ ይጠየቅ
ዛሬውኑ ይንገረን ከእኛ ማን እንዲልቅ
ንገረን መምህር ሆይ! ከእኛ ማን ይበልጣል?
ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ዛሬ ይታወቃል”
ብለው ሲማከሩ ጴጥሮስ አንዱ ነበር
እሱ እንደሚበልጥ ሳይገባው ጥርጥር

ጨካኝ ነው መምህሩ፣ መልስ ሲሰጣቸው
መች እንደጠበቁት እርሱ ሆነላቸው
”ፊተኛ ለመሆን የሚወድ ቢኖር
ራሱን እንደባሪያ ዝቅ አድርጎ ይቁጠር
የሰው ልጅም መቷል ይህን ሊተገብር”
”አሃ!” አለ ጴጥሮስ ራሱን እያከከ
በተሰጠው ምላሽ ልቡ እየታወከ
”ጭራሽ ተፈለገ እንድሆን አገልጋይ
ታናሽ እንዴት ብሎ ይሆናል የበላይ?”

ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ እንዲህ ሆነ
መምህሩ መሞቻው ጊዜው ተፋጠነ
ያን ጊዜ ማታ ላይ አንድ ላይ ሰብስቦ
ወደዳቸው ሁሉን ወደርሱ አቅርቦ
ራሱን ዝቅ አድርጎ እግራቸውን ሲያጥብ
አብሮ ተዋረደ ያ የጴጥሮስም ልብ
እራት አበላቸው ደቀመዛሙርቱን
እያስተማራቸው አይቀሬውን ሞቱን
እንዲህም አላቸው
”እረኛው ሲመታ በወንበዴዎች
ሁላችሁም ናችሁ እኔን ካዷዎች”
ጴጥሮስ ተነሳና ምሎ ተገዝቶ
”ቱ! አዳሜ ቢክድህ ዉለታህን ረስቶ
እኔ ካደረኩት አይንጋልኝ መሽቶ”
አለ በፉከራ ራሱን ተመክቶ
መምህሩ ግን አለው
”እንግዲህ ሁሉንም ይለየዋል ዶሮው!”

# እንዲህ ...

ይህንን ብሏቸው
ይዟቸው ተጓዘ ወደ ተራራ ላይ
ይተጉ እንደሆነ አብረው በመጸለይ
ወይ ፍንክች! በዚያ በጭንቅ ቀን ሁሉም
ማንኅላጀጅ!
ይይዛቸው ጀመር አንድ ሰዓት ሳይፈጅ

ከጊዜ በኋላ እንዲህ እንዲህ ሆነ
እረኛው ተመታ ሁሉም ተበተነ
እስኪ ፈልጉልኝ ጴጥሮስ የት እንዳለ?
ያውና ተቀምጦ እሳት እየሞቀ
ከኢየሱስ ጋር መሆን ስለተሳቀቀ
ሰራተኛ ጠየቀችው ማን እንደሆነ እሱ
የጌታውን ወሬ ስሙን እያነሱ
ጴጥሮስ ተነሳና ምሎ ተገዘተ
በጠያቂዋ ፊት እንዲህ እየዛተ
”ቱ! ሁሉም ካገለለው ከዚህ እርጉም ሰው ጋር
አብረህ ነበርክ ተብዬ እኔ ግን ልጠርጠር
በሉ ዝም በሉ ሰው እንዳይሰማችሁ
እኔ ይህንን ሰው አላውቅም ባካችሁ”
ብሎ እየረገመው ጴጥሮስ ኢየሱስን
መላ ሲደረድር ሰዎቹን ሊያሳምን
ትላንትና ኢየሱስ እንደተናገረው
”ኩኩ..” ብሎ ጮኸ መሰከረ ዶሮው!

አበበ ምህረት
አዲስ አበባ
(ክፍል ሁለት በሚቀጥለው ቁጥር ይቀጥላል)

## ጌታ ረዳቴ ነው

ጌታ ፡ ረዳቴ ፡ ነው ፡ በድካሜ
መስቀሉን ፡ ይዣለሁ ፡ ተሸክሜ
ልለየው ፡ ብሞክር ፡ ልከደው
ፍቅሩ ፡ ግድ ፡ ይለኛል ፡ እንዳልተወው

ሕይወቴ ፡ ሲደክም ፡ ሲዝልብኝ
ረዳት ፡ የሌለኝ ፡ እኔን ፡ ሲመስለኝ
ጌታ ፡ በክንዶቹ ፡ ያነሳኛል
ደረቁን ፡ ሕይወቴን ፡ ያረካዋል

አንዴ ፡ በሸለቆ ፡ እንዲያ ፡ ሳለቅስ
አንዴ ፡ በተራራ ፡ ስፈነጥዝ
የመስቀሉን ፡ መንገድ ፡ ስለማመድ
ብዙ ፡ ትምህርት ፡ አለው ፡ ብወድ

እኔ ፡ ተስፋ ፡ አልቆርጥም ፡ እቆማለሁ
የሕይወቴን ፡ መንገድ ፡ መርጫለሁ
እደክማለሁ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ አልፈራም
የሕይወትን ፡ እራስ ፡ አልክደውም፡፡

ደረጀ ከበደ

ቋሚ አምድ

# እንደምን አደጋችሁ?

በፓስተር መላክ አለማየሁ



ካለፈው የቀጠለ

ባለፉት ሁለት ክፍሎች በመንፈሳዊ ሕይወታችን ስለ ማደግ ጠቅለል ባለ መልኩ መግቢያ የሚሆንን ሃሳብ ለማየት ሞክረናል። የፈጠረንና የዋጀን እግዚአብሔር ለእኛ ያለው አላማ እለት እለት ወደ በረከቱ ሙላት እንድናድግ መሆኑ ቃሉ አስተምሮናል። እንዲሁም፣ በጸጋ ማደግ የሚከቱትን ሦስት አቅጣጫዎች እንደሚያቅፍ ተመልክተናል:-

- በማምለክ ማደግ-ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የፍቅር ህብረት ይመለከታል
- ደጋፊ በመሆን ማደግ-በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ካሉ ወንድም እህቶቻችን ጋር ያለንን ህብረት ይመለከታል
- ግዴታችንን በመወጣት ማደግ-ከእግዚአብሔር ርቀው ያሉትን ፍቅሩን በማንጸባረቅ ወደ እርሱ ማደምን ይመለከታል

እነዚህ ሦስቱ የእድገት አቅጣጫዎች ማደግ በሚለው ምጻረ ቃል ሊታውሱ ይችላሉ።
በዚህ የጥናታችን ክፍል ደግሞ ወደ ክርስቶስ መስቀል ትኩረታችንን እናደርጋለን። ጌታችን በመስቀል ደሙን በማፌሰስ የከፈለው ድንቅ መስዋእትነት፣ ከላይ በተጠቀሱት ሦስት አቅጣጫዎች ለማደግ እንድንችል እንዴት ሃይል እንደሚሆንን እናጠናለን።

**የመስቀሉ ሃይል በማምለክ ለማደግ**
አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር ፍቅር የምንሰጠው ምላሽ እንደመሆኑ፣ የመለኮትን ፍቅር በጥልቀት መረዳት በማምለክ ለማደግ አማራጭ የሌለው ጎዳና ነው። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ደግሞ ተወዳዳሪ ባልተገኘለት ድምቀት የተገለጠው በመስቀል ላይ አምላካችን ራሱን ለእኛ አሳልፎ በሰጠበት ጊዜ ነበር። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ:- "ነገር ግን ገና ሃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" ሮሜ 5:8

በመስቀል ላይ የተገለጠው ይህ ፍቅር ወደ እርሱ የሚያቀርበንና ከእርሱም ጋር የጠበቀ ህብረት እንዲኖረን አቅም የሚሆነን ነው። በመስቀል ላይ ከጌታችን አጠገብ ተሰቅለው ከነበሩት ሁለት ውንበዴዎች መካከል አንደኛው ይህንን ፍቅር ለአፍታ ባስተዋለ ጊዜ በንስሃ ልቡ ተሞልቶ ከአምላኩ ጋር የነበረውን ግንኙነት አደሰ። (ሉቃ 23:40-43)። እኛም የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን ከከፋ መንገዳን ተመልሰን፣ ለሃጢአት ጀርባችንን ሰጥተን፣ የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም በሙሉ ልባችን እንገዛለታለን። ከሚጠፋውና ከሚያጠፋው የዚህ አለም ሃሳብ ይልቅ የእርሱን መንግስት እንመኛለን።

**የመስቀሉ ሃይል ደጋፊ በመሆን ለማደግ**
በክርስቶስ መስቀል የተገለጠው ፍቅር የጥልን ግድግዳ በማፍረስ እርስ በርሳችን በፍቅር እንድንተሳሰርና እንድንደጋገፍ የሚያስችለንንም ሃይል ይሰጠናል።
"ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ራሱ ነውና፤… ጥልን በገደለበት በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ። ኤፌ. 2: 14, 16

ጌታችን በመስቀል ላይ ሆኖ በብዙ ጣእርና ስቃይ ከተናገራቸው ሰባት ቃላት መካከል ሁለቱ ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳዩ እንደሆኑ እናያለን። ሊያድናቸው የመጣው የገዛ ወገኖቹ በጠላትነት በመስቀል ላይ ሰቅለው በፊቱ ሆነው ሲዘባበቱበት ስለ እነርሱ እንዲህ አለ:- "አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ሉቃ 23:34። በእርሱ ላይ በደረሰው ልቡዋ በሃዘን ተሰብሮ ከመስቀሉ ግርጌ ለነበረችው እናቱ ለማርያም "አንቺ ሴት ሆይ፤ ልጅሽ ይኸው" አላት፤ ደቀ መዝሙሩንም፣ "እናትህ ይህችው" አለው። (ዮሐ 19: 26፣ 27) ይህ ንግግሩ ከራሱ ስቃይ ባሻገር ለሌሎች በፍቅር በማሰብ ያደረገውን የፍቅር ድርጊት የሚያሳይ ነው።

በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስንኖር፣ ወዳጆች እንዲሁም ጠላቶች ይገጥሙናል። በመስቀል ላይ የተገለጠው ፍቅር ታዲያ ጠላቶቻችንን ይቅር እንድንል፣ ወዳጆቻችንንም እንድንከባከብ ግድ ይለናል። የቀራኒዮ ፍቅር የገባት ነፍስ ቂም አትይዝም። በራስ ወዳድነት አትዋጥም። ይልቁንም ያገኑ ፍቅር ለሌሎች ታካፍላለች።

**የመስቀሉ ሃይል ግዴታችንን በመወጣት ለማደግ**
የመስቀሉ ፍቅር የገባው ሐዋርያው ጳውሎስ "ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ፣ ወንጌልን የምሰብከው ግዴታዬ ስልሆነ ነው" ብሎ ይጽፋል። ታዲያ ወንጌልን ለሌሎች በማካፈፍል እንዲህ እንዲተጋ ግድ የሚለው ምን እንደሆነ ሲጽፍ ደግሞ እንዲህ ይላል:- "የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል" 2 ቆሮ 5:14፣ 15። በእርግጥም በመስቀሉ የተገለጠው የመለኮት ፍቅር ሃይል የራቁትን የሚያቅርብ፣ የቀርቡትንም ሩቅ ያሉትን ይፈልጉ ዘንድ የሚያነሳሳ ሃይል አለው። በመስቀሉ ግርጌ የነበረው የጌታ ደቀ መዝሙር ዮሐንስ፣ ከመስቀሉ በፊት የሰማርያ ሰዎች የጌታን አገልግሎት ለመቀበል ባልፈለጉበት ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲበላቸው የተመኘቶ ነበር (ሉቃ 9:54)። በመስቀል ላይ ያየው ፍቅር ሲለውጠው ግን እንዲህ ብሎ ጻፈ:- "እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው፤ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም።" (1 ዮሐ 2:2) ለአለም ሁሉ የፈሰሰው ደም ወደ አለም ሁሉ እንድሄድና ይህንን ድንቅ የምስራች እንድናበስር ግድ ይለናል።

በመንፈሳዊ ህይወታችን በጸጋው ለማደግ ወደ ክርስቶስ መስቀል መመልከት፣ በዚያም ላይ የተገለጠውን የእርሱን ፍቅር የዘወትር ሃሳባችን ማድረግ አማራጭ የሌለው ጎዳና ነው። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት እድገታችን የተስተጓጎለብን ብናር፣ ዛሬ ወደ መስቀሉ እንመለከት ዘንድ መንፍስ ቅዱስ ይጠራናል። ከዚያም መለኮታዊ የሆነው የፍቅር ሃይል በአምልኮ ህይወታችን፣ ከወንድሞቻችን ጋር ባለን ህብረትና በተሰጠን ተልእኮ ይሄውም ወደ አለም ሁሉ ሄደን በጨለማ ለተዋጡ ሁሉ ብርሃኑን የማሳይትን ሃላፊነታችንን በመወጣት ረገድ እንድናድግ ያግዘናል። ጌታ እለት እለት ያሳድገን!

**"በነገር ሁሉ እናድጋለን"**

**ኤፌሶን 2:15**

”ድር ቢያብር አንበሳ ያስር”



## Appeal from our Seventh day Adventist brothers and sisters in Israel

Dear brothers and sisters,

We are writing this urgent message to you from the promised-land of Israel. You probably have heard by now that our beloved brother and spiritual leader, **Pastor Getu Kassa**, died in a tragic car accident on September 8, 2016. Pastor Getu was an effective and dedicated evangelist in Ethiopia. From 2003 to his untimely death in 2016, he served as pastor of an Ethiopian Adventist congregation in Israel. Pastor Getu worked tirelessly to secure a place of worship for us, and he visited, encouraged, and taught young and old to come to the throne of grace and worship the creator with us.

It has been very difficult to function without Pastor Getu's leadership and vision, and we are currently in grave danger to lose the momentum he built among Ethiopian Seventh day Adventists here in Israel. We have been blessed to worship together for over fourteen years, but we are facing serious challenges to continue serving and worshipping our Lord. We are writing this letter to appeal to everyone from anywhere and everywhere to join us in prayer. We are also appealing for financial support. We have a burning desire to continue Pastor Getu's legacy and vision.

The main point of this writing is this: We need our own place of worship. It has become increasingly difficult to continue renting a worship place. The only solution is to buy or build our own modest house of worship. Please join us in this sacred vision. It would be a shame to discontinue what Pastor Getu and his Ethiopian Adventist Fellowship put in place. There are roughly 100 Ethiopian Seventh day Adventists in Israel. 50 of us actively participate in worship every Sabbath. With God's help and your active participation, our goal is to grow our small congregation, and share the gospel of our Lord Jesus Christ with the larger Ethiopian community in Israel. Thank you very much, and God bless.

Sincerely,
Your brothers and sisters in Israel.

Seventh-day Adventists in Israel

President's Office

Abraham Lincoln Street 4-6
P. O. Box 592
Jerusalem 91000
ISRAEL

Telephone: +972 54 54 33 411
Email:
roger.robertsen@netvision.net.il

Jerusalem, 15 January 2018

**TO WHOM IT MAY CONCERN**

The Rehovot Ethiopian Seventh-day Adventist Church in Israel is in need of a new place to worship.

Rehovot is located about 20 minutes' drive from the road where the Ethiopian Eunuch was converted when Philip explained the Gospel to him. This is therefore in many ways where the message among Ethiopians began almost 2000 years ago, and now this church is calling on Ethiopians everywhere to help consolidate the work in this historic place.

The Rehovot congregation has a good potential for growth:

a) There are many children and young people in the church, and the members are actively involved.
b) There are about fifty inactive SDAs of Ethiopian origin in Israel. We hope to reach these.
c) There are approximately 150,000 Israelis of Ethiopian origin living in Israel. We now hope to reach as many as possible among these.

The Israel Field of Seventh-day Adventists is a small Mission Field, not a Conference or a Union. We do not have the financial resources to acquire new places of worship for our local congregations. Financial support from outside of Israel is therefore an absolute necessity, and this congregation now needs such funds. Donations are therefore very much needed and appreciated.

If you are wondering "How can I help, and how can I donate", then see the next page.

In a Christian Ethiopian context this is a unique historical place, and new SDA church facilities can actually have historical and momentous importance for Ethiopians worldwide as this is where they have their Christian roots – it is where it all began!

With kind and Christian regards,

Roger Robertsen
President

## HOW TO DONATE:

All donations should be sent to the Israel Field. They may be given through the regular SDA organizations to the Israel Field, or transferred directly to the Israel Field. Please mark all donations: "Rehovot New Church, Israel Field."

When you donate, then please inform us about the amount and the date you send/transfer the donation. If possible, you should scan and send the wire transfer document to us. In this way, it is easier for us to trace the donation and make sure it arrives safely without any problems.

Once the donation enters our bank account, we will credit the donation to the church account of Rehovot Ethiopian.

Any questions? Please contact Pastor Julio Mendez, the Treasurer of the Israel Field:

Julio.mendez@netvision.net.il
Telephone: +972 54 200 5202

## Bank Transfer to Dollar Account

Details enabling efficient effect of transferring funds from abroad to the Israel Field US Dollars account in Mercantile Discount Bank Ltd.

| | |
|---|---|
| **Bank Name:** | **Mercantile Discount Bank Ltd** |
| **Branch Name:** | **Agron St., Jerusalem Israel** |
| **BIC or Swift Code:** | **BARDILITXXX** |
| **Clearing Code:** | **IL017646** |
| **Account Number:** | **646-968013-036307** |
| **Beneficiary Name:** | **Seventh Day Adventist** |
| **IBAN NUMBER:** | **IL260176460000002036306** |

**The BIC Code is the Swift Code.**
**BIC means Bank Identification Code**

## Bank Transfer to Shekel Account

Details enabling efficient effect of transferring funds from abroad to the Israel Field shekels account in Mercantile Discount Bank Ltd.

| | |
|---|---|
| **Bank Name:** | **Mercantile Discount Bank Ltd** |
| **Branch Name:** | **Agron St., Jerusalem Israel** |
| **BIC or Swift Code:** | **BARDILITXXX** |
| **Clearing Code:** | **IL017646** |
| **Account Number:** | **646-000000036307** |
| **Beneficiary Name:** | **Seventh Day Adventist** |
| **IBAN NUMBER:** | **IL870176460000001036302** |

**The BIC Code is the Swift Code**
**BIC means Bank Identification Code**

## *የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ (2 ቆሮ 3:3)*

ስለ ደብዳቤ ሲነሳ ብዙዎቻችን ወደ ድሮ ትዝታ 'ይድረስ ሰላምታዬ ለምወድህ/ሽ.....' ተብሎ በሚጀመርበት ዘመን የምንወሰድ ይመስለኛል። አሁን ያለንበት በሰከንድ ልዩነት በemail ና የተለያዩ የተክኖሎጂ ውጤቶች የምንገናኝባቸው መንገዶች እኛ ጋ ከመድረሳቸው በፊት ከእኛ ርቀው ያሉትን ወዳጆቻችንን የምናገኛቸው በስልክ ካልሆነ በደብዳቤ ነበር። አንዳንዴ እንደ ቦታው ርቀት ሳምንታትን ወይም ወራትን ተቀባዩ ጋር ለመድረስ ቢወስድም በትዕግስት ከመጠበቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበረም። በተለይ የፍቅር ደብዳቤ ከሆነ ደግሞ የተላከልን ደብዳቤ እስኪደርስ አንድ ሳምንት ከቆየ ወራትን የዘገየ ይመስለናል ወሩም እንደ አመት ነው የሚረዝምብን። እንደ ምንም ደብዳቤው ሲደርስ የሚሰማን ስሜት የተለየ ነው። ገና የላኪውን ስም በማየት የልብ ትርታችን እጥፍ ይሆናል። እንዶርፊን ና የተለያዩ ሆርሞኖች ሰውነታችንን ሲወሩ ነው ያ ስሜት የሚሰማን ይላሉ ሳይንቲስቶቹ። ደብዳቤው እንደ ምንም ተከፍቶ ሲነበብ ደግሞ የተጻፈበት ወረቀት ወረቅትነቱ ይቀርና የላኪውን ድምጽ የሚያሰማ፣ ፊታቸውን የሚያሳይ ሆኖ በምናብ ይዟችሁ ይጓዛል። እንዲህ የተጠበቀ ደብዳቤ አንዴ ብቻ ተነቦ አይጣልም። በዶ/ር እንደታዘዘ መድሃኒት በቀን ሁለቴ ወይም ሦስቴ ካልሆነም ማታ ከመኝታ በፊት አንዴ ይነበባል። ከዛም ለወደፊት እንደአስፈላጊነቱ ለማንበብ በጥንቃቄ ይቀመጣል። ከዛ ደግሞ የደብዳቤውን መልስ ለመጻፍ የምንወስደው ጊዜ ና የሚያልቀው የወረቀት ብዛትስ!

እንግዲህ በሁለት በሚዋደዱ ሰዎች መሐል ስለሚላላክ የፍቅር ደብዳቤ ይህን ያህል ካልን ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች 'ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ' ሲል ምን አይነት ደብዳቤ ነው ብለን መጠየቅ ግድ ይለናል። ጳውሎስም የጻፈው ባጭሩ ስለ የፍቅር ደብዳቤ ነው። ይህን ለማረጋገጥ የላኪውን ስም ማወቅ በቂ ነው- ስሙ/መገለጫው 'ፍቅር' ነው - እግዚአብሔር ፍቅር ነው ይላል 1 ዮሃ 4:8,16 ላይ። ስለዚህ ጳውሎስ እንደጻፈው 'የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ' የሚለውን 'የፍቅር ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ' ብለን መተርጎም እንችላለን ማለት ነው።

ግን ምን አይነት ፍቅረኛ ነው?
ይህን ጥያቄ ለመመለስ መጽሃፍ ቅዱስ ይህንን አፍቃሪ አምላክ ምን ብሎ እንደሚገልጸው እንመልከት።

- ለወደዳቸው ያለውን ሁሉ የሚሰጥ የማይሰስት፤ ራሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ የሚወድ አፍቃሪ - ...አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ሁሉ እንዲሁ ወዷልና( ዮሃ 3:16)
- ለመውደድ ሁኔታ የማይወስነው፣ በኃጥዓት ከቆሸሸ ማንነታችን የወደደን - ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ለኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።(ሮሜ 5:8)
- ምህረቱ ለዛለለም የሆነ ወዳጅ - እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና ምህረቱ ለዘላለም ነውና። (መዝ 136:1)
- በአባትነት ጥልቅ ፍቅር የሚወድ - የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን (1 ዮሃ 3:1)
- ከወዳጆቹ መለየትን የሚጠላ፣ለዘላለም ከልጆቹ ጋር መኖርን የሚመኝ አፍቃሪ - በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ (ዘጸ 25:8)። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ (ዮሃ 14:2-3)።

የዚህን አፍቃሪ ማንነት ለመዘርዘር ጊዜና ሁኔታውም አይበቃንም ፣ በቃላት ብዛትም አይገለጽም፣ እውነቱን ለመናገር ፍቅሩን አይተናል ብንልም ጥልቀቱ አልገባንም፤ የዘላለም ጥናታችን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም ትዕግስቱ ና ምህረቱ ለዘላለም ቢሆንም ልቡ የቆሰለበት አፍቃሪም ነው። ሆሴዕ 11ን ስናጠና እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሚያሳየውን ፍቅርና የሃዘን ቃላትን እናነባለን። 'እስራኤልን ሕጻን በነበረ ጊዜ ወደድሁት' (ቁጥ 1) በማለት ይጀምራል። 'በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው' (ቁጥ 4) ፣....ሕዝቤም ከእኔ ይመለሱ ዘንድ ወደዱ' (ቁጥ 7) ከዚህም የተነሳ 'ልቤ በውስጤ ተናውጣለች (ቁጥ 8) ብሎ ሃዘኑን ሲገልጽ እንመለከታለን።

እንዲሁም ደግሞ ትንቢተ ኤርምያስ 8:18 ላይ 'ስለ እስራኤል ሕዝብ ሃዘኔ የማይጽናና ነው ልቤም በውስጤ ደክሟል' ይላል። ሃዘኑም ልክ እንደ ፍቅሩ ጥልቅ ይመስላል! ይህን ሁሉ መስዋዕትነት የሚከፍልላቸው ልቡ እስኪደክም ድረስ የሚያዝንላቸው ለምን ይሁን? ማን ናቸው የዩኒቨርስ ሁሉ ፈጣሪ እንዲህ የሚሰቃይላቸው?

የደብዳቤው መድረሻ አድራሻ ፣በኃጢአት ለወደቀው፣ ለጥፋት ለተዘጋጀው ለሰው ልጅ፣ 'ለዓለም ሁሉ' ነው! መቼም ደብዳቤ አጠገብ ላለ ሰው አይጻፍም ሩቅ ለሚኖር ወዳጅ እንጂ።

ታሪኩ ባጭሩ እንዲህ ነው - እግዚአብሔር በመጀመርያ የሰውን ልጅ በአምሳያው ሙሉ አድርጎ ፈጥሮ በኤደን ገነት ባማረ ቦታ አስቀመጣቸው። ልክ እንደ ቤተሰብ ከነርሱ ጋር ይገናኝና ያወራ፣ ይንከባከባቸው ነበር።እነሱም በየቀኑ ድምጹን መስማት፣ ፊቱን ማየት ናፍቆታቸው ነበር። ግን ያ የጥንቱ ጠላት ይህንን ግንኙነት ለማፍረስ በሔዋን በኩል ኃጥዓትን ዘራ። የሰው ልጅ በራሱ ምርጫ የእግዚአብሔርን ህግ በመተላለፍ ከአምላኩ ከወዳጁ ርቆ ሄደ። የኃጥአት ግርግዳ አባትን ከሚወዳቸው ልጆቹ ለየ፣ በአካል ፊት ለ ፊት ተገናኝተው ማውራት ሲያከትም ክርስቶስ ደብዳቤ መጻፍ ግድ ሆነበት። በተለያዩ የኃይማኖት አርበኞችና ነብያት በኩል ደብዳቤውን ለጠፉት ልጆቹ መላክ ጀመረ። ከዛም የእስራኤልን ህዝብ የተለዩ ሕዝብ እንዲሆኑና ሌላውን አለም ከእውነተኛ አምላካቸው ጋር እንዲያስተዋውቁ ግልጽ ደብዳቤ እንዲሆኑ መረጣቸው። የእስራኤል ሕዝብ ግን ጥሪያቸውን፣ ደብዳቤነታቸውን ረሱት። መልዕክቱን ለራሳቸው ይዘው አቆዩት። የኑሮአቸውም ዘይቤ የላኪው እግዚአብሔርን ማንነት አጎደፈ። የሚያነቧቸው ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ጨካኝ፣ ቁጡ፤ የሚያዳላ አምላክ አድርገው ቆጠሩት። ምህረቱ የበዛ እግዚአብሔር ግን አልረሳቸውም ነበር፣ በየጊዜው ነቢያትን እየላከ ማንነታቸውን፣ የአለም ብርሃን መሆናቸውን ያስታውሳቸው ነበር። ለአጭር ጊዜ ከእንቅልፋቸው የነቁ ቢመስሉም እግዚአብሔር አምላካቸውን በአህዛብ ፊት መካድና መርሳትን የየቀን ተለምዷቸው አደረጉ።

እንግዲህ የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ (ገላ 4:4) እግዚአብሔር ከነቢያትም ሁሉ በላይ የሆነውን እራሱ አምላክ የሆነውን አንድያ ልጁን ላከ። የተረሳው ደብዳቤ እንደገና የሚታደስበት፣ አቧራው የሚራገፍለት፣ ለሰው ሁሉ ብርሃን የሚበራበት (ዮሃ 1:9)ጊዜ ደረሰ። ኢየሱስም በራሳቸው እጅ የነበረውን እነሱ ሸክም ያደረጉትን ሕግና ነቢያትን ሳይሽር በፍቅር አስውቦ ለጠፉት ወገኖቹ አቀረበ። የእስራኤል ሕዝብ ግን አልተቀበሉትም። እራሱን የደብዳቤውን ደራሲ ተሳስተሃል አሉት፣ የደብዳቤውን መልዕክት በራሳቸው በተሳሳተ አተረጓገም ሊያነቡለት ሞከሩ። እንግዲህ እግዚአብሔር ሁሌም ሰው አለውና ልባቸው የተነካ ብርሃኑን ያዩት፣ ዓይናቸው የተከፈተላቸው ደግሞ ኢየሱስን ተከተሉት። እንደ አዲስ ደብዳቤውን አሁን ገና አነበቡት። እንደ ኤማሁስ መንገደኞች የፍቅር ደብዳቤው ሲከፈትላቸው ልባቸው ተቀጣጠለ (ሉቃ 24:33)፣ እራሱ የደብዳቤው ደራሲ ኢየሱስ የደብዳቤውን መልዕክት በልባቸው ላይ አኖረ። በደሙም ማህተም ደብዳቤውን አጸደቀው። የእስራኤል ህዝብ የሠሩትን በደል እንዳይደግሙ የተሰጣቸውን ደብዳቤ ለጠፉት ወገኖች እንዲያስተላልፉ አስጠነቀቃቸው። ‘እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ’ (ማቴ 28:19) ብሎ ስልጣን ሰጣቸው። ደቀ መዛሙርትም በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ደብዳቤውን ማስተላለፍ ቀጠሉ። ብዙ አህዛብም/ነፍሳትም እነሱን በማንበብ መዳን ቻሉ። ደብዳቤውም ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፉን ቀጠለ። አሁንም ሰይጣን የደብዳቤውን መልዕክት ከሰው ልጅ አእምሮ ለማጥፋት ትግሉን በሌላ መልክ ጀመረ። የደብዳቤውን እውነት የተቀበሉ ሁሉ ለብዙ ዓመታት ሲሰደዱ ሲገደሉ ቆዩ። በጥቂቶች የእምነት ጀግኖች አሁንም የተደበቀው ደብዳቤ ግልጽ ወጣ። እናም በመጨረሻ እኛ ጋ ደረሰ። ነገሩ እንደ የቅብብሎሽ ሩጫ ነው። የመነበብ ተራው አሁን የኛ ነው። እኛም እንደ እስራኤል ህዝብ ለዓለም ምሳሌ እንድንሆን የእርሱንም በጎነት እንድንናገር የተመረጠን ትውልድ፣ የንጉስ ካህናት አደረገን (1ጴጥ 2:9)። ችግሩ ግን በግልጽ የምንነበብ የክርስቶስ ደብዳቤዎች መሆናችንን እኛስ አውቀናል ወይ? ለተላከላቸው ነፍሳት እያደረስን ነው ወይስ ደብቀን አስቀምጠናል?

እስቲ ስለ አንድ ልጁ ለረጅም ዘመናት ከቤት የጠፋበትን አባት እናስብ። ልጁ ከአባቱ በጣም ርቆ ከመሄዱ የተነሳ የቤታቸው አቅጣጫ ጠፍቶበታል፣ አባቱንም ረስቶታል። ታዲያ ይህ አባት አገልጋዮቹ ልጁን ፈልገው አግኝተው እንዲሰጡት ደብዳቤ አስይዟቸው ይሰዳቸዋል። ይህም ደብዳቤ የአባቱን የማይለወጥ ፍቅር የሚገልጽ፣ ልጁ ወደ ድሮ ቤቱ እንዲመለስ የሚማጸን፣ አባቱ ልጁ ላጠፋው ጥፋት ይቅር እንዳለው የሚገልጽ ነው። እንዲሁም መመለስ ሲወስን ወደ አባቱ ቤት የሚመራ ካርታም ጭምር ተልኮለታል። እነዚህ አገልጋዮቹ ግን ከቤት በፈቃደኝነት ቢወጡም ዓላማቸውን ረሱት። ስለ ላካቸው አባትም ሆነ ስለ ጠፋው ልጅ ግድም አልሰጣቸውም። ይህ አባት ልጁን ለማግኘት ያለውን ከባድ ጉጉት እያወቁ መንገድ ላይ አላማቸውን የሳቱ አገልጋዮች የአባትየውን ሃዘን እጥፍ አደረጉት። ከሁለቱም ያጣ አባት ሆነ፤ ልጁም የተላከለትን የይቅርታ ደብዳቤ አግኝቶ ወደ ቤቱ አልተመለሰም፣ አገልጋዮቹም መጨረሻቸው ጥፋት ሆነ።

እኛስ? ወንጌልን ለዓለም ሁሉ የማድረስ አደራ፣ በቤት ውስጥም ይሆን በውጪ የጠፉትን የአባታችንን ልጆች የመፈለጋችን አደራ ምን አድርገን ይሆን? በአኗኗራችን ለነፍሳት መጥፋት ወይስ መዳን ምክንያት እየሆንን ነው? የክርስቶስን አስደናቂ ፍቅር እንደኛ ያልታደሉ ነፍሳት በኛ ውስጥ ሲንጸባረቅ አይተው ይመኙት ይሆን ወይስ የእዚአብሔርን ስም የምናሰድብ፣ ፍቅሩን ደብቀን ፍርዱን ብቻ የምናወራ፣ በግልጽ ኃጢአት እየተመላለስን የእግዚአብሔር መንፈስ ከኃጢአት ሁሉ ነጻ እንደሚያወጣ በህይወታችን እየካደን ነው ያለነው? ጊዜው አሁን የኛ ነው። ከዓለም ጋር በመመሳሰላችን ለዓለም ምሳሌ መሆን ካቃተን፤ እኛም ዓላማችንን ረስተናል ማለት ነው። ዓላማውን የሳተ አገልጋይ ደግሞ መጨረሻው ጥፋት ነው። ስለዚህ እኛም ልክ ጳውሎስ ለቆሮንቶስን ሰዎች ‘እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ (1 ቆር 11:1) እያለ ሲማጸናቸው እንደ ነበር፤ በገላትያ 4:19 ላይ ደግሞ ‘ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል’ ሲል ጥልቅ የሆነውን ምኞቱን እንደሚገልጽላቸው ከሁሉም የበለጠ ምኞታችን ብቸኛው ምሳሌያችንን ክርስቶስን መምሰል መሆን አለበት። ያኔ እውነተኛ የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤ ለመሆን እንበቃለን። ደብዳቤውን የማስተላለፍ አደራም በእኛ አያበቃም፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ መሰራጨቱን ይቀጥላል፣’ ....ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል (2 ጴጥ 3፡ 8-9) የሚለው ተስፋም ፍጻሜ ያገኝ ና ኢየሱስም ቶሎ ይመለሳል። ማንነታችንን እንድናውቅ፣ መልካም ደብዳቤ የመሆን አደራችንን እንድንወጣ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛልን!

ተመስገን ታምሩ

ደቡብ አፍሪካ

## ማስታወቂያዎች

### የአውሮፓ አቀፍ ኮንፍራንስ

በየሁለት አመቱ የሚደረገው የአውሮፓ አቀፍ ኮንፍራንስ 4—10 ኦገስት 2019 በስወድን አገር ይካሔዳል። ማንኛውም የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አማኞችና ወዳጆች እንዲሁም በአድቬንቲስት ትምህርት ቤቶች የተማሩ የቀድሞ ተማሪዎች ሊሳተፉበት ይችላሉ። የበለጠ ለመረዳት ዳንኤል ኃይለማርያምን ጠይቁ።

### ለአገራችን እንፀልይ

በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈግሉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ **ምድራቸውንም እፈውሳለሁ**። 2ዜና 7:14

## ዳግማዊ ሰንሰለት



ሰንሰለት ከብዙ አመታት ፀጥታ ቦኃላ እነሆ መልኳን ቀይራ መታለች። ድሮ በወረቀት ታትማ በፖስታ ትላክ ነበር። አሁን ግን በኢሜይል ብቅ ትላለች።

ይህች የኤሌክትሮኒክ መጽሔት በአለም ላይ ተበታትነን ላለነው የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አማኞችና ወዳጆች እንዲሁም በአድቬንቲስት ትምህርት ቤቶች ለተማሩ የቀድሞ ተማሪዎች በየሶስት ወሩ በኢሜይል ትበተናለች።

አላማችን ለመጽናናት፤ ለመደጋገፍ፤ ሃሳብና መልእክት ለመለዋወጥ ስለሆነ አንባቢ ሁሉ በዚህ መንፈስ እንድታነቡትና እንድትተባበሩን እንጠይቃለን።

”**ዳግማዊ ሰንሰለት**” እንዲላክላችሁ ከፈለጋችሁ ወይም እንዲላክላቸው የምትፈልጉ ካሉ ከዚህ በታች ባለው የኢሜይል አድራሻ የኢሜይል አድራሻ ብትልኩ ሰንሰለትን እንልክላችኋለን።

## የኛ ለኛ በኛ

”ዳግማዊ ሰንሰለት” የኛ መጽሔት ለኛ የተዘጋጀና በኛ የሚዘጋጅ መጽሔት ነው። ስለሆነም የመጽሔታችን ይዘት በተመለከተ የሁላችን ትብብር ያስፈልጋል። አንድን መጽሔት ተፈላጊና ወቅታዊ የሚያደርገው የአንባቢያን ተሳትፎ ነውና አንባቢያን ሁሉ ለዚች መጽሔት የሚሆኑ የጽሑፍ አስተዋጻኦችን ማበርከት ይችላሉ። የተላከውን አስተዋጻኦ መጠቀምና አለመጠቀም ግን የአዘጋጁ መብት ነው።

ሃሳባችሁንና አስተያየታችሁን እንዲሁም ጽሑፍ ካላችሁ ለአዘጋጁ እንድትልኩ በትህትና እንጠይቃለን። አስተያየታችሁን፡ ምስክርነቶችን፡ ግጥሞችን፡ ገንቢ ጽሁፎችን፡ መንፈሳዊ መልክቶትችን፡ በደስታ እንቀበላለን።

# ሰንሰለት

C/O Daniel Hailemariam
Ekebyholmsvägen 170
76291 Rimbo, Sweden

+46 737762407
**hailemariam6@hotmail.com**



አዘጋጅ
ዳንኤል ኃይለማርያም (ፓስተር)

